# ከእግዚአብሔር ፍቅር

... እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ ፡ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ። ኢሳ 48 ÷ 17
God's Love, P.O.Box 6734, Lee's Summit MO 64064. E-mail – glnlm@ethiogodslove.org አዘጋጅ መላኩ ትዕዛዙ

www.ethiogodslove.org 4ኛ ደብዳቤ 2005 እአአ 4th Quarter 2007


ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፥ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል። ትንቢተ ኢሳይያስ 54÷13

# አሥራት



መስጠት የዕምነት ውጤት ነው። ሰው ከልቡ ለሚወደው ነገር ገንዘቡን ይሰጣል። ገንዘቡን በታማኝነት የሚያ ወጣበት ነገር ደግሞ በሰውየው ሕይወ ት ውስጥ ትልቅ ሥፍራ ያለው መሆኑ ን ያሳያል።

እንግዲያው በዚህ አስተሳሰብ ሲታ ይ እግዚአብሔር በሕይወቱ ትልቅ ሥፍራ የያዘለት ሰው ለእግዚአብሔር ሥራ ቃሉ በሚያስተምረው መሠረት ይሰጣል ማለት ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ የእግዚአብሔር ሰው ከእግዚአብሔር የተማረና ሁሌም የሚማር ነው። ይህም የመጽሐፍ ቅዱ ስ ትምሕርት ነው። ስለዚህ የመስጠት ን ጥቅም ያስተውላል።

እግዚአብሔር ሲባርክ አሠራሩ አ ስገራሚ ነው። የሚሰጥ ይቀበላል። በ ቸርነት ለሚሰጥ ደግሞ ይበዛለታል። ለሚሰጥ ሰው ተመልሶ የሚሰጠውም ዓይነት በዓይነት ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ለእግዚአብሔር ሥራ የሚ ሰጥ ሁሉ ግን በምንም ዋጋ ሊተመን የማይችል መንፈሳዊ በረከት ይቀበላል። ይህንንም ስንል ቁሳዊ በረከት አይቀበ ልም ማለት ሳይሆን፥በምድራዊው ነገ ር የታመነውን ያክል በሰማያዊውም በረከት ስለሚታመን ከመልካም ነገር ሁሉ አይጐድልም ለማለት ነው።

ይህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። በምድ ራዊው (ጊዜያዊ) ያልታመነ ግን በሰማ ያዊው ጸጋ ሊታመን እንዴት ይችላል

በቸርነት እግዚአብሔር ከሁሉ ይ በልጣል። ለሰውም መልካም የሆነውን ሁሉ መስጠት ይፈልጋል። በእግዚአ ብሔርም ዘንድ እንደ ሰው ልጅ የተወ ደደ ፍጥረት የለም። ለዚህ ማስረጃ የ ሚሆነው፥ስለ ሰው ልጅ ኃጢአት አን ድያ ልጁን አሳልፎ መስጠቱ ነው። ል ጁንም በመስጠት አርአያ የሆነው መ ስጠትን መረዳት ለሰው ልጅ እጅግ አ ስፈላጊ መሆኑን ያሳያል። አሠራሩም

> "ስጡ ይሰጣችሁማል፡በምትሰፍሩበት መስፈ ሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና ፡ የተጨቆነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪ ያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል።" የሚል ነው። (የሉቃስ ወንጌል 6 ÷ 38)

ለመሆኑ አሥራት መውጣት የሚገባ ው እንዴት ነው?

## * ከፍሬ በኩራት፡-

"እግዚአብሔርን ከሀብትህ አክብር፥ ከፍሬህም ሁሉ በኩራት፡" (ምሳሌ 3÷9) አምላክህ እግዚአብሔር አስችሎህ ከምታገኘው ገቢህ የመጀመሪያው (በ ኩራት) ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ሥ ራ ማካሄጃ መሰጠት አለበት። ይህም ከማንኛውም (ከሁሉም) ገቢያችን መሆን እንዳለበት ቃሉ እንዲህ ያስረዳል።

"ከእርሻ ምርትም ሆነ ከዛፍ ፍሬ፥ ማንኛውም ከምድሪቱ የሚገኝ አሥራ ት የእግዚአብሔር ነው ፤ ለእግዚአ ብሔርም የተቀደሰ ነው።..... ከቀንድ ከብቶች፥ከበጎችና ከፍየሎች መንጋ የ ሚወጣው አሥራት፡ከእረኛ በትር በታ ች ከሚያልፉት አሥረኛው እንስሳ ይሆናል፤ይህም ለእግዚአብሔር የተቀ ደሰ ነው። (ሌዋውያን 27÷30-31)

## * ተመጣጣኝ አሥራት፡-

(proportional tithing)

ለእግዚአብሔር ሥራ የምንሰጠው አሥራት ከገቢያችን ጋር ተመጣጣኝ መሆን ይገባዋል። ይህም ማለት ለምሳ ሌ ከአሥር ጠቅላላ ገቢ አንድ፥ከመቶ አሥር እና ከሺህ መቶ ማለት ነው።

እግዚአብሔር ከሺህ ብር መቶ የሚ ሰጠውንና ከአሥር አንድ የሚሰጠው ን በእኩልነት ይመለከታል። ምክንያ ቱም እርሱን የሚገደው በታማኝነት መታዘዛችን ስለሆነ ነው። ሺ ብር እያ ገባ ዘጠና የሚሰጠው ግን እንደ ታማኝ ሊቆጠር አይችልም። ተመጣጣኝ አሰ ጣጥ ግን ሐብታምና ድሀ አይለይም። (ኦሪት ዘሌዋውያን 27÷30-34 ያንብቡ)

## * አየተጎዱ አሥራት መስጠት

(sacrificial tithing)

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ከጉድ ለታችን እንድንሰጥ ይፈልጋል። ሳይ ተርፍ ከራስ አጎድሎ ለእግዚአብሔር ሥራ መስጠት የሚከተሉትን ሁለት ሁኔታዎች ያጠቃልላል። አሥራትን ላለማስተላለፍ ብሎ የሚፈልጉትን ነገ ር ትቶ ወይም ለሌላ ጊዜ አስተላልፎ መስጠትና ለመስጠት ሲሉ አኗኗርን መለወጥ ወይም ማስተካከል ናቸው።

በመስዋዕትነት ስንሰጥ ስጦታችን ክ ቡር ይሆናል። ቃሉ እንዲህ ይላል፡- "በብዙ መከራ ተፈትነው ሳሉ የደስ ታቸው ብዛትና የድህነታቸው ጥልቅ ነት የልግስናቸውን ባለጠግነት አብዝ ቶአል፤ እንደ አቅማቸው መጠን፡ ከአ ቅማቸውም የሚያልፍ እንኳ ወደው እንደ ሰጡ እመሰክርላቸዋለሁና። (2 ቆሮ 8÷2-3) ሌላው ከዚህ ጋር

በተጨማሪ መጠቀስ ያለበት ጥሩ ምሳሌ ደግሞ:- ነቢዩ ኤልያስን ትመግብ ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዛት ባልቴት ታሪክ ነው:: በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 17÷ 8-16 እንደተጻፈው (አንብቡት) "ትመግብህ ዘንድ አንዲት ባልቴት አዝዣለሁ" (ቁ 9) በማለት ለኤልያስ ሲናገር እንመለከታለን:: በዚያው ክፍል የባልቴቲቱን ኢኰኖሚ ሁኔታ ከራሷ ምስክርነት ስናነብ ደግሞ:- በዚህ ዘመን ሥራ አጥ የሚባል ያክል በጣም ድሀ መሆኗን በመሐላ ተናግራለች:: (ቁ12) ጌታ እግዚአብሔር ግን ነቢዩን እንድትመግብ አዘዛት::

ባልቴቲቱ ጨክና በመታዘዟ ግን፤ጌታ እግዚአብሔርም÷ነቢዩም÷ ባልቴቲቱም ደስተኞች የሆኑበትን ሁኔታ እናስተውላለን:: ባልቴቲቱ ባትታዘዝ ኖሮ ግን ነቢዩ ከዚያ በፊት እንደሆነው በቁራም ቢሆን መመገቡ አይቀርም:: እርሷና ልጇ ግን ያላቸውን ሲጨርሱ በርሀብ ይሞቱ ነበር:: ከተረፈው መስጠት ለንፉጎችና ለማይታዘዙት እንኳ ፈተና አይሆንም፤ ከጐደለው መስጠት ግን የታማኝነት መለኪያ ነው:: በአሥራታችን ታዛዥና ታማኞች ከሆንን በኋላ የቀረልን ተባርኮ ይብቃቃል? ፈጽሞ አይጎድልም:: የሚጎድል ቢሆን ፈትኑኝ ባላላ ነበር::

## * በቋሚነት መስጠት:-

(regular giving)

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያክል መስጠት እንደሚገባን ብቻ ሳይሆን÷ምን ያክል አዘውትረን መስጠት እንደሚገባንም ጭምር ሲያመለክት:- "በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን" ይላል:: (1 ቆሮ 16÷2) ይህም ሲባል አንዳንድ ጊዜ ኑሮ አይከብድም ማለት አይደለም:: ሆኖም አሥራትን አለማውጣት፣ የሚያስከትለው መንፈሳዊ ኪሳራ ማንም በራሱ ላይ መፍረድ የማይገባው ውጤት ነው::

## * በደስታ መስጠት:-

Cheerful giving

ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሰው መቀበል ደስ ይላል:: ማለትም አለበት::መስጠት ግን ከስሜት ሁሉ በላይ የሆነ የነፍስ ሐሴት ይሰጣል::መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ሥራና ለሰው በመስጠት መታዘዛችንን በመጠቀም ዕምነታችንን ያበረታል:: ያም ደግሞ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጥልቅ ወደ ሆነው በረከት የምንገባበት የጽድቅ ጉልበት ይሆናል::

"ይህንን እላለሁ:- በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል÷በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደገሞ ያጭዳል:: እግዚአብሔር በደስታ የሚዘራውን (የሚሰጠውን) ይወዳልና:..." (2 ቆሮ 9÷6-7)

በመስጠት ያለውን ደስታና ትርፍ አለማወቅ አሳዛኝ ነገር ነው:: ዐይናችን ተከፍቶ ብናይ ÷ የስንቶቻችን በረከት በራሳችን ንፍገትና ስስት ታግዶና ተጠራቅሞ ተቀምጧል?

## * ለታይታ ያልሆነ መስጠት:-

ለእግዚአብሔርም ሥራ ሆነ ለሰው ስንሰጥ ዓላማችን እግዚአብሔርን በመታዘዝ ማስደሰት መሆን አለበት:: የሰው ማድነቅ ጊዜያዊ÷ የእግዚአብሔር ደስታ ግን ዘላለማዊ ዋጋ እነዳለው በማወቅ÷ የራስን ቸርነት ከማወጅ መቆጠብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው:: ቃሉ እንዲህ ይላል: "ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ ያለዚያ በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም::" (ማቴ 6÷1) ይህም የልብን ሁኔታ ሮስመልክቶ እንጂ አንዳዶች እንደሚሉት÷ አሥራትን በድብቅ ካልሰጠን ማለት አይደለም:: ምን ያክል አሥራት እንደምንከፍል ከቤተክርስቲያ መሪዎች መደበቅ ይልቁን መሪዎቻችንን እንዳያውቁ ያደርጋል:: ይህም ደግሞ የደከሙትን መቀስቀስ እንዳይቻል በማድረግ ሁሉን ይጎዳል::

## * አሥራት መስጠት:-

"ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልዑል እግዚአብሔርም የተባረከ ነው አለው:: አብራምም ከሁሉ አሥራትን ሰጠው::" (ኦሪት ዘፍጥረት 14 ÷ 20)

ይህ ቃል፡ ከአሥር አንድ ወይም ከየአሥሩ አንዳንድ ማለት እንደሆነ ግልጽ ነው::

ሁሉን የሰጠን እግዚአብሔር ነው:: እርሱ ከምድር ፍሬ አሥሩን በአደራ ይሰጠናል:: እኛም ከአሥር አንዱን መልሰን ለሥራው እንሰጣለን:: እርሱ ደግሞ ከመታዘዛችን የተነሣ የቀረውን ዘጠኙን ነቀዝ ሆነ ልዩ ልዩ ተባይ እንዳይባላብን ያዝዛል:: ለዚህ ነው በአሥራት ያልታመኑ ሰዎች ከቶ የማይሞላላቸው:: በአሥራታቸው ታማኞች የሆኑት ግን ገቢያቸው ብዙ ባይሆንም እንኳን ሁሌ የማይጎድላቸው ብሩክ ኑሮ ሲኖሩ ይታያሉ:: ጌታ ባርኮላቸዋልና ያላቸው ጥቂት ይበረክታል::

"እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም፤... ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምሮ ከትዕዛዛቴ ፈቀቅ ብላችኋል፤አልጠበቃችኋቸውም፤ወደ እኔ ተመለሱ፤እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ" ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት:: "እናንተ ግን፡ የምንመለሰው እንዴት ነው ትላላችሁ? ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል:: እናንተም የሰረቅንህ እንዴት ነው ብላችኋል:: በአሥራትና በበኩራት ነው:: እናንተ ይህ ሕዝብ ሁሉ÷ እኔን ሰርቃችኋልና በእርግማን ርጉሞች ናችሁ:: በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን አሥራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ (ቤተ ክርስቲያን) አስገቡ ፤ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ፥ በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር:: ስለ እናንተ ነቀዙን እገሥጻለሁ፥ የምድራችሁንም ፍሬ አያጠፋም፤..." (ትንቢተ ሚልክያስ 3÷ 6-11)

በአሥራት ላይ ያለን አመለካከት ዕምነታችን የቱን ያህል ዕውነተኛ መሆኑን ለራሳችን ሊያሳየን የሚገባ መስታወት ነው:: ምክንያቱም ያመነ የተጠመቀ ይድናል÷በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን ያለውና÷እግዚአብሔርን ከሐ

ብትህ አክብር÷ ከፍሬህም ሁሉ በኩራ ት፡ ያለው ቃል እኩል የታመነ ስለሆነ ነው፡፡

> “እግዚአብሔርን ከሐብትህ አክብር ÷ ከፍሬህም ሁሉ በኩራት” (መጽሐፈ ምሳሌ 3÷9)
>
> “ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል፡፡ እናንተም የሰረቅንህ በምንድር ነው? ብ ላችኋል፡፡ በአሥራትና በበኩራት ነው፡፡ እናንተ÷ይህ ሕዝብ ሁሉ÷እኔን ሰርቃችኋልና በእርግማን ርጉሞች ናችሁ፡፡ በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን፡ አሥራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አግቡ፤ … በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ ÷ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር (ሚልክያስ 3÷8-10)

በአሥራትና በመስጠት ታማኝነት ወደ ተትረፈረፈ በረከት የምንገባበት ዓመት ይሁንልን። በጌታ በየሱሰ ክርስ ቶስ ስም፤ አሜን፡፡

---

www.ethiogodslove.org

የድረ ገጽ አገልግሎታችንን በመጎብኘት ÷ በዓመታት የተሰራጩትን መልክቶቻችንን ማንበብ ይችላሉ። እትም ማሰራጨትም ሆነ ለጥናት መጠቀም ይቻላል። ኢ-ሜይል አድራሻችን እነሆ፡-
glnlm@ethiogodslove.org

# ንዴትና ቁጣ



*አንድ ተናዳጅና ቁጡ ልጅ ነበረ፤ ከዚህም ባሕሪዩ የተነሣ አብረውት የ ሚኖሩት እጅግ ይቸገሩ ነበር፡፡ በተና ደደ ጊዜ ሁሉ ከአፉ የሚወጣው ቃል ቤተሰቡን ያስጨንቅ ነበር፡፡ የራሱን ንዴት የሚያበርድ የመሰለውን ሁሉ ከማድረግ ወይም ከማለት አይቆጠብ ም ነበር፡፡ ቤተሰቡ እና ጎረቤቶቹ ምን ማድረግ እንደሚሻል ግራ ይገባቸው ነበር፡፡*

*ከዕለታት አንድ ቀን ግን የልጁ አባ ት አንድ ሃሳብ መጣለት፡፡ እርሱም ልጁን ጠራውና አንድ ከረጢት ሙሉ ምስማር ሰጠው፡፡ ጨምሮም አንድ ጥ ሩ መዶሻ ሰጠው፡፡ ከዚያም ልጄ ሆይ! ከዛሬ ጀምሮ÷ ንዴትህ በመጣብህ ቁጥ ር÷ ወደ አጥሩ ሮጠህ አንድ ምስማር በአጥሩ ላይ በመዶሻው ቸንክር፡፡ ለእ ያንዳንዱ ንዴትህ አንዳንድ ምስማር ቸንክር፡፡ ምስማሩም እስኪያልቅብህ ድረስ በተናደድህ ቁጥር እንዲህ አድ ርግ አለው፡፡*

*ልጁም እንደታዘዘው ማድረግ ጀመ ረ፡፡ በመጀመሪያው ዕለት ሰላሳ ሰባት 37 ምስማሮችን በአጥሩ ላይ ቸንክሮ ዋለ፡፡ ከዚያም እየደከመውና እየሰለቸ ው ስለሄደ በየቀኑ እየቀነሰ መጣ፡፡ በዚህ ጊዜ ÷ ምስማር ሲቀጠቅጥ ከመ ዋል ንዴቱን መቆጣጠር እንደሚቀል ማስተዋል ጀመረ፡፡*
*በመጨረሻም ሙሉ ቀን ሳይናደድ መ ዋሉን ባየ ጊዜ ሄዶ ለአባቱ ነገረው፡፡*

*የልጁም አባት የሆነውን ካስተዋለ በኋላ መልካም ልጄ÷ አሁን ደግሞ ሂ ድና÷ ንዴትህን ተቆጣጥረህ በዋልህበ ት በእያንዳንዱ ቀን÷ ከቸነከርኻቸው ምስማሮች አንዳንድ ምስማር ንቀል፡፡ ስትጨርሰም መጥተህ አስታውቀኝ ሲል አዘዘው፡፡ ልጁም ከብዙ ቀናትና ድካም በኋላ ወደ አባቱ ቀርቦ ምስማ ሮቹን በሙሉ ነቃቅሎ መጨረሱን በ ታላቅ እፎይታ ነገረው፡፡ ከዚያም አባ ትየው መልካም ልጄ÷ ተከተለኝ ብሎት አብረው ወደ አጥሩ አመሩ፡፡*

*አጥሩም ዘንድ እንደ ደረሱ አባትየው የአጥሩን ሁኔታ ከአስተዋለ በኋላ ልጁን እንዲህ ሲል ማነጋገር ጀመረ፡፡ ልጄ ጎበዝ ነህ፡፡ ሁሉንም እንዳዘዝኩህ ፈጽ መሃል፡፡ ነገር ግን አጥራችን ወንፊት መስሎአል፡፡ ተመልሶም እንደ ነበረው ጤነኛ አጥር አይሆንም፡፡ ታስተውላለ ህ? ተናደድሁ ባልህ ቁጥር ከአፍህ የምትወረውረው ቃል ሁሉ በሰዎች ላይ ቁስል ያስቀራል፡፡ ያም ቁስል ቢ ድንም እንኳ ተመልሶ እንደ ነበረው አይሆንም፡፡ ይቅርታም ብትጠይቅና÷ ሰዎችም ይቅር ቢሉህ እንኳ ÷ ቁስሉ እንዳልነበረ አይሆንም፡፡ የቃላት ቁስል ከጎራዴ ቁስል ያነሰ አይደለምና፡፡*

*ወዳጅ እንደ ዕንቁ መከበር አለበት፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ዕንቁም የማይተካከለ ው ወዳጅ ይገኛል፡፡ ወዳጅ በሀዘን ቀን ያጽናናል፡፡ ያሰብኸው መልካም ነገር እንዲከናወንልህ ያበረታታሃል፡፡ የልብ ትካዜ ካለብህ ሊያዳምጥህ ይፈቅዳል፡፡ መልካም ያደረግህ እንደ ሆነ ያመሰግ ንሃል፡፡ የዘንህ አስተዛዝኝ ÷ የደስታህ አዳማቂ ይሆንልሃል፡፡ ስለዚህ ስትናደ ድ÷ለወዳጅህ የፍቅር ጥንቃቄ አድርግ* ሲል መከረው ይባላል፡፡

የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል፡ “ቁጡ ሰው በስንፍና ይሠራል፤አስተዋ ይ ግን ይታገሣል፡፡” (መጽሐፈ ምሳሌ 14÷17)

“ቁጡ ሰው ጠብን ያነሣሣል፤ትዕግሥ ተኛ ሰው ግን ጸጥ ያሰኘዋል፡፡”
(መጽሐፈ ምሳሌ 15÷18)

“አሁን ግን እናንተ ደግሞ ቁጣንና ንዴትን ክፋትንም÷ ከአፋችሁም ስድ ብን የሚያሳፍርንም ንግግር እነዚህን ሁሉ አስወግዱ” (ቆላስይስ 3÷8)

“መራርነትና ንዴት ቁጣም ጩኸት ም መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ፡፡ እርስ በርሳ ችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ ÷ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይ ቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ፡፡”
(ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4÷31-32)

---

# የመንግሥተ ሰማይ ሚስጢር

መንግሥተ ሰማይ መግባት የማይመ ኝ ሰው የለም፡፡ በጣም ደግ በመሆን÷ የቤተክርስቲያን አባል በመሆን÷ ብዙ በመጸም ወይም ገዳም በመግባት የሚ

ታገሉ አሉ:: እነዚህ ሁሉ መልካም ድርጊቶች ቢሆኑም በእግዚአብሔር ፊት ግን ለመንግሥተ ሰማይ ብቁ አያደርጉም:: የሚከተለው መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ከተመረመረ በኋላ የተጠናቀረ እግዚአብሔር በዘመኑ መጨረሻ የገለጸው÷የመንግሥተ ሰማይ መግቢያ ሚስጢር ነው::

1ኛ/ እግዚአብሔር ይወደናል::

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ <u>እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና</u>::"

(የዮሐንስ ወንጌል 3÷16)

2ኛ/ ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ነው::

"ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤" (ሮሜ 3÷23)

3ኛ/ ኃጢአት ሞትን ያስከትላል::

"የኃጢአት ዋጋ ሞት ነውና" (ሮሜ 6÷23)

4ኛ/ የኃጢአታችን ዕዳ ተከፍሏል::

"ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና"

(ሮሜ 5÷6)

5ኛ/ ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ ዕዳችንን የከፈለ መሆኑን አምኖ መቀበል::

"በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም::"

(የዮሐንስ ወንጌል 3÷36)

6ኛ/ *ያመኑትን መናገር:-*

"ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና" (ወደ ሮሜ ሰዎች 10÷9)

--------------------------------

# *የጊዜ ገደብ*

*"በተወደደ ሰዓት ሰማሁህ፡በመዳንም ቀን ረዳሁህ ይላልና፤እነሆ÷ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው፤ እነሆ የመዳን ቀን አሁን ነው::" (2 ቆሮንቶስ 6÷2)*

*"መከሩ አልፎአል÷በጋው ሄዶአል÷ እኛም አልዳንንም::" (ት/ኤርምያስ 8÷20)*

## *በርግጥ ድነሃል? ድነሻል?*

*"ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት÷ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበላቸው÷ ..." (ዕብራውያን 9÷27)*

# *ጊዜው አሁን ነው*

*"እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት÷ ቀርቦም ሳለ ጥሩት÷ክፉ ሰው መንገዱን÷ በደለኛም አሳቡን ይተው፤ ወደ እግዚአብሔርም ይመለስ÷ እርሱም ይምረዋል÷ይቅርታውም ብዙ ነውና ወደ አምላካችን ይመለስ::"*

*( ኢሳይያስ 55÷6-7)*

## *እምቢተኛነት ኃጢአት ነው::*

*"... እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው እንዴት እናመልጣለን?"*

*(ዕብራውያን 2÷3)*

*"እግዚአብሔርን የማያውቁትን ÷ ለጌታችንም ለእየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል፤ በዚያም ቀን በቅዱሳኑ ሊከብር ...በሚያምኑት ሁሉ ዘንድ ሊገረም ሲመጣ÷<u>(እምቢተኞች) ከጌታ ፊት ፡ ከኃይሉም ክብር ርቀው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ</u>::"*

*(2 ተሰሎንቄ 1÷8-10)*

## ዛሬ ግን ተስፋ በደጅህ ነው

<u>የእግዚአብሔር ፍቅር</u> የሆነው ጌታ እየሱስ ክርስቶሰ በዚህች ደብዳቤ አማካይነት እንዲህ ይልሃል::"እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ÷ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ÷ ወደ እርሱ እገባለሁ፡ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ፡ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል::"

(ራዕይ 3÷20)

እንዲህ ነው:: "እየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር÷ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና÷ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና÷በአፉም መስክሮ ይድናልና::"

(ሮሜ 10÷9-10)

---

**ፀሎት:-**ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! ይህን ያነበብኩትን መልዕክት፡ በዕምነት ተቀብያለሁ:: መንግሥተ ሰማይ ሚስጢር ሆኖብኝ እንዳልቀር ልቤን ሰጠሁህ:: አንተም ወደ መንግሥተ ሰማይ ተቀበለኝ:: ስለ ስምህ ስትል:: አሜን::

*ጻድቅና ታማኝ የሆንኸው ጌታ ቅዱስ እግዚአብሔር ሆይ! ይህንን ጸሎት በዕምነት የጸለየች ነፍስ ሁሉ÷ በማይዋሸው ቃልህ መሠረት ÷ ወደ መንግሥተ ሰማይ ተቀባይነት ስለተሰጣት አመሰግንሃለሁ:: በጌታዬ በየሱስ ክርስቶስ ስም፤ አሜን::*

---



መላኩ ትዕዛዙ

# እንኳን ለጌታችን ልደት መታሰቢያና ለአዲሱ ዓመት አደረሳችሁ:: ብሩክ ዓመት!

የተወደዳችሁ ወዳጆቻችን:- እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ:: አዲሱ ዓመት የአዲስ ተሰፋና የበረከት እንዲሁም የብዙ ፍሬ ዓመት እንዲሆንላችሁ ፀሎታችን ነው::

በ1999 እአአ የጀመርነውን ይህንን አገልግሎት በጌታ ቸርነትና በቅዱሳን ፀሎት ርዳታ እስካሁን ይዘን መጥተናል:: በጠራን ጌታ ታማኝነት ጥቂት ለውጦችና ዕድገት አድርገናል የድረ ገጽ አገልግሎታችን ተገልጋዮች ቁጥር የሚያበረታታ ነው:: ጌታ እንዲህ ከከበረብን በታላቅ ትኅትናና በደስታ እንተጋለን:: ለምሳሌ:- በኅዳር 06፡ <u>6145</u>÷ በጥቅምት <u>6183</u>÷ በመስከረም፡ <u>5091</u>÷ በነሐሴ፡ <u>4926</u>፡ በሐምሌ 4411፡ በሰኔ ወር፡ 5786፡ በግንቦት <u>7273</u>፡ ሚያዝያ <u>6111</u>፡ መጋቢት <u>5121</u>፡ ጎብኚዎችን አገልግለናል:: ጸጋው እንደ በዛልን መጠን÷ በ2007ም እንተጋለን:: ፀልዩልን:: በገንዘብ ለምትደግፉን የግብር ተቀናሽ ደረሰኝ መስጠት እንችላለን:: ብሩክ አዲስ ዓመት ይሁንላችሁ:: በጌታ ፍቅር::

*እየሱስ ጌታ ነው::*

*ጌታ ይባርካችሁ::*